የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

መጋቢት 7 ቀን 2002 ዓ.ም.

# ወያኔ በአርሶ አደሩ ይወገዳል እንጂ ለምን አይወገድ!!

ይድረስ

የረሃብ ሰለባና በተለያዩ በሽታዎች ተጠቂ ለሆናችሁ፡ ሰብዓዊ መብታችሁ ለተረገጠና ፍትህ ርትዕ ተነፍጓችሁ፡ በድህነት ወለል ላይ ሆናችሁ እየተሰቃያችሁ ኑሯችሁን ለመግፋት ለተዳረጋችሁ፡ ነፃነታችሁን ለተነፈጋችሁ ብዙሃን አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ሆይ!!

ይህንን መልዕክት የሚያስተላልፍላችሁ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) በምን አይነት የኑሮ ሁኔታ ላይ እንደምትገኙ ከልቡ በጣም የሚገነዘበው ብቻ ሳይሆን፡ ይህንን አሳዛኝና አስከፊ ሁኔታ በየቀኑ ለመቋቋምና ብሎም ጨርሶውኑ ከሱ ለመገላገል የምታደርጉትን እንቅስቃሴ በሚገባ የሚደግፈው ነው። ይህንን ሲል ደግሞ በመካከላችሁ አብሮ በመኖር ችግራችሁ ችግሩ፣ ስቃያችሁ ስቃዩ፣ ሀዘናችሁ ሀዘኑ፣ ደስታችሁን የራሱ ደስታ አድርጎ በመካፈሉ እንጂ እራሱን ከላይ እናንተን ከታች በመመልከት ለፖለቲካ ፍጆታ ሲል የሚናገረው እንዳልሆነ ትገነዘቡለታላችሁ። ይህ መለያ ጠባዩ እንደሆነም ከናንተ በላይ ምስክር የሚሆነው ማንም የለም።

የቀን ተቀን ኑሯችሁን ለመቋቋም ስትሉ የምትዳክሩት፡ በጣም አድካሚና ጊዜ ፈጅ ቢሆንም ጥራችሁ ግራችሁ ከምታርሱት የእርሻ መሬት የምታመርቱት ምርትም ሆነ የቤት ከብቶችን አርብታችሁ የምታገኙት ጥቅም ከድካማችሁ ጋር የሚመጣጠን እንዳይደለ በሀዘንና በቁጭት የተገነዘብነው ሐቅ ነው። ለዚህ ምክንያቱ ቀዳሚው አንዳንዶቹ ሊመጻደቁባችሁ እንደሚጥሩት ስንፍና የተጠናወታችሁ ሳትሆኑ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻችሁ ስላልተከበሩላችሁ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በምታርሱት መሬት ላይ የግል የማይገሰስ የባለቤትነት መብት በወያኔ ሕግ የተነፈጋችሁ በመሆናችሁ ነው። ይባስ ብሎ ወያኔ፣ አርሶ አደሩ መሬትን በግል ንብረትነት (በባለቤትነት) ከያዘ መሬቱን በመሸጥ ወደ ጭሰኝነት ይወርዳል፣ ይመለሳል እናም "መሬት የመንግሥትና የሕዝብ ሀብት" መሆን አለበት የሚል የማደናገሪያና 'የጭራቅ መጣብህ' ማስፈራሪያ ጅራፉን ቢያጮህም፡ እሱ ራሱ እናንተን በግዴታ የሱ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ጥገኛ ማድረጉን ግን በቀን ሕይወታችሁ የምትኖሩት ነውና ሊደብቅለት የሚችል አይደለም። በተለይ ይህ ድርጊቱ ከአምባገነናዊ አገዛዙ፤ እኩልነትን ካለማስፈኑ፤ በመልካም አስተዳደር እጦት የተነሳም የናንተ በፖለቲካው ውሳኔ ተሳትፎ ካለመኖር ጋር ተዳምሮ ችግሩን ምን ያህል የከፋ

እንዳደረገባችሁም በግልጽ የምታዩት ነው። ወያኔ በአምሳሉ ባደራጃቸው ኩባንያዎች አማካኝነት በሌለ ዴሞክራሲ አጅቦ ከናንተ ጋር የፈጠረው ግንኙነት፣ በስም የተለየ ይምሰል እንጂ ካለፉት ገባርና አስገባሪ ጋር ተመሳሳይ መሆኑንም እንዲሁ የምትገነዘቡት ነው። ይህ ብቻ አይደለም።

ለእርሻ ምርቶቻችሁ ማደግ አስፈላጊ የሆኑትን የማዳበሪያና የምርጥ ዘር አቅርቦት በተሟላና በቂ ጥናት በተደረገበት ሁኔታ በየወቅቱ ማግኘት አለመቻላችሁ፤ ሰጡሁ የሚለውን የምርጥ ዘር እንኳ ለምን ያህሎቻችሁ በምን መስፈርት ተመርኩዞ እንደተሰጣችሁ፤ ምን ያህሎቻችሁ በርግጥም ውጤታማ እንደሆናችሁ፣ ካልሆናችሁ ደግሞ ምክንያቱ ከተጨባጭ መረጃ ጋር ቀርቦላችሁ ባጠቃላይ እነዚህን ሁሉ በግልጽ ተወያይታችሁ የበኩላችሁን መፍትሄ ለማፈላለግ የአቅማችሁን እንዳትጥሩ የመናገር መብታችሁን አጥታችኋል። ሕገ መንግሥቱ በሚለው ሰነድ ውስጥ ያካተታቸውን እንኳ ተጠቅማችሁ ፍላጎታችሁንና ጥቅማችሁን ለማስከበር እንዳትጋፈጡት፣ በነጻ ያለምንም ጣልቃ ገብነት የመደራጀት መብታችሁን ገፏችኋል። ለምታረባቸው የቤት ከብቶችም ቢሆን እንደ ወረርሽኝና ሌሎችም በሽታዎች እንዳይጠቁ ክትባትን ሲጠቁ ደግሞ በቂ ለእንስሳት የሕክምና አገልግሎትና በዚህም ላይ የተመሰረተ ትምህርት እንዲሁም መድኃኒት ባለማግኘታችሁ ለሕልፈተ ሕይወት በሚዳረጉት ከብቶቻችሁ የተነሳ የሚደርስባችሁ ተደራራቢ ስቃይ የሚያንገበግበን ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ከዓመት ወደ ዓመት እየዘለቀ የሚሄደውን የመሬት መሸርሸር ለመግታት፤ ለደን እንክብካቤና ለመስኖ መስፋፋት፡ ለመደለያ ሳይሆን በርግጠኝነትና በተጨባጭ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት፡ በናንተ ፍላጎትና ጥቅም እንዲሁም ተሳትፎ ተግባራዊ የሚደረግበት፤ ከባሕላዊና ከደካማ አስተራረስ ለመውጣት እስከዛሬ ድረስ ሁኔታው አልተመቻቸላችሁም። በሰው ሠራሽ የተፈጥሮ መዛባትና በቀላሉ ፈውስ ሊያገኙ በሚችሉ በሽታዎች በለጋ እድሜያችሁ እንደ ቅጠል መርገፍ ሌላው ቅልጥ ብሎ የሚታይ አስከፊ ዕውነታ ነው። ያም ሆኖ በየዓመቱ እየጨመረ ከሚሄደው የገበሬው ማህበረሰብ ክፍል ቁጥር አንጻር (ለእርሻ የሚሆን መሬት ባልጠፋበት) ለማረስ የሚደለደልላችሁ የመሬት መጠን ግን እየቀነሰ መሄዱ የገቢ ምንጮቻችሁ እየመነመነ መምጣት ምክንያት እንደሆነ የምታውቁት ነው።

ወያኔ በቅርቡ በመቀሌ ከተማ የአርሶ አደሮች ፌስቲቫል ዝግጅት እንዳደረገውና አርሶ አደሩንና አርብቶ አደሩን ዋና ተገኔ እያለ ስለናንተ ሊመጻደቅ ቢጥርም ለእድገታችሁ በጣም ወሳኝ የሆነ፤ ስለዋጋ መረጃ የመስጠትም ሆነ ከናንተ



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

መረጃ የመቀበል ሥልጣኑን በጁ በማድረጉ ጥራችሁ ግራችሁ ትንሽም ብትሆን ያፈራችሁትን የድካም ፍሬ በመንጠቅ የአገዛዙ አባላትና የሱ ደጋፊዎች እየከበሩበት ይገኛል። ታዲያ ይህ ብዝበዛ ካልሆነ በምንስ ይተረጎማል? ይህ የሚያረገውና የሚለው ሁሉ ለራሱ የፖለቲካ ፍጆታ ከመሆን በስተቀር እውነትነት የሌለው ነው። በችግር ጊዜ ፈጥኖ ሊደርስላችሁ ፍላጎት የሌለው፤ የረሃብ ጥቃት ሰለባ መሆናችሁን ግን ለግል መጠቀሚያ እያደረገ የባዕዳን ተመፅዋች እንድትሆኑና ሰብዓዊነታችሁን እንድታጡ ማድረጉ የሚያመለክተውም የዚሁኑ ነፀብራቅ ነው።

የኤኮኖሚ መሠረታችሁ ዝናብን ተከትሎ የሚዋልል መሆኑ የምታውቁት ነው። የዝናብ ነገር አስተማማኝ መሆኑ ዘመናት አልፎታልና በወቅቱ ካልጣለ የእህል መዝራት ጊዜው ያልፍና ወይንም ደግሞ የተዘራውም በቂ ዝናብ ባለመገኘቱ የድርቅ ሰለባነት ስለሚከተል የሚቀመስ ጠፍቶ ለድርቅና ለረሃብ የምትጋለጡበት ወራቶች በርካታ ናቸው። ዝናብ ከሚገባው በላይ ሲገኝ ደግሞ ለመስኖ እንዲሆን እንኳን የተዘጋጀ መገደቢያ ባለመኖሩ የተዘራውን ከማበላሸቱም ሌላ የመጀመሪያው ገፈት ቀማሽ እናንተ ስትሆኑ ይህም ለሌላው የሕብረተሰብ ክፍልም የሚደርስ መሆኑ የታየ ነው። ይህን ሁሉ ተቋቁማችሁ ከምታገኙት ምርት ላይ የተለያዩ ግብሮችን ብትከፍሉም የትምህርት፣ የጤና፣ ንፁህ ውሃና የመሳሰሉና እንዲሁም ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶችን በአግባቡ አታገኙም። ውሃ ለመቅዳት በየዕለቱ በርካታ የሰዓታት ጉዞ ዛሬም የተለመደ ሆኖባችኋል።

ግብርናን ማዕከል ያደረገ ስትራተጂ በሚል የቀመረላችሁ መርሃ ግብር፡ የናንተን የልብ ትርታ ያልኮረኮረ መሆኑን ከናንተ በላይ የሚያውቀው የለም። ይባስ ብሎ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተቀባበላችሁ ከምታርሱበት መሬት ብቻ ሳይሆን ለግጦሽ መጠቀሚያ የምትገለገሉበት ሰፋፊ መሬቶች ለባዕዳን በጣም ርካሽ በሆነ ዋጋ እየቸበቸበ መሆኑን በአይናችሁ የምትመለከቱት ነው። በዘመናዊ ዘዴ መሬታችሁ እየታረሰ የሚገኘው ምርት ግን በረሃብ አለንጋ እየተጠበሳችሁ ላላችሁት ማስታገሻ ሳይሆን ለራሳቸው ሕዝብ ፍጆታ ወደ መጡበት ሀገር እያጓጓዙት ሲሆን ለእይታ ለባለሥልጣኖቻቸው በገጸ በረከት የቀረቡ መሆናቸውንም የምታስታውሱት ነው። እናንተ እየተራባችሁ ባዕዳኖች በገዛ ሀገራችሁ የተመረተ ምርት ለምቾት ሲጠቀሙበት ማየት ምን ያህል ብሄራዊ ክብራችንና ማንነታችን በመለስ አገዛዝ እየተዋረደና ዋጋ ቢስ እየሆነ መምጣቱን የሚያመላክትና በጣምም የሚያሳፍረንም ነው። ይሉኝታ ሲጠፋ መዳረሻው ሀገር እንደ ሀገር ሕዝብም እንደ ሕዝብ ከውርደት መውደቅንም የሚጠቁመን ነው። ከሁሉ በላይ የሚያበሳጨው ወያኔ በሚከተለው ፖሊሲ የተነሳ የምግብ ችግር



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

የመኖሩ ጉዳይ ነው። ስንዴ ለማምረት እውቀቱም፣ ልምዱም፣ ችሎታውም እያላችሁ እናንተ ወደጎን እየተገፋችሁ አሁንም ስንዴን ያውም በሚሊዮን የሚቆጠር ኩንታል በውጭ ምንዛሪ እየተገዛ ወደሀገር የመግባቱ ሁኔታ ነው። እነዚህ ኢንቬስተሮች ናቸው የሚባሉት እናንተን እየበደለና አብሮ እየዘረፈ ካለው ቡድን ጋር ወዳጅ በመሆናቸው ተቃውሞ ባቀረባችሁ ቁጥር ያደረሱባችሁን በደል የምትረሱት አይሆንም። እንዲያውም ወደፊት በትግላችሁ ወያኔን ለመጣል እንቅስቃሴ ብትጠነስሱ ለማስተጓጎል ወደኋላ የማይሉ ለመሆናቸው በሌላ ሀገሮች የታዩ ሁኔታዎች ሳይቀር ይመሰክራሉ። አስፈላጊውን የገንዘብ ድጎማና ፖለቲካዊ ድጋፍ ቢያገኙ ሀገር በቀል የሆኑ ኢትዮጵያውያን እነዚህ ባዕዳን የሚሰሩትን ለመስራት የሚያንሱ አለመሆናቸው ወደኋላ መለስ ብሎ ያለ ታሪክን ብናይ በቂ ምሳሌዎች ማግኘቱ የሚቻል ነበር።

እነዚህ ባዕዳኖች እናንተን ከገበሬነት ወደ ተራ ሰራተኛነት ቢለዉጧችሁም (ይህም ካለፍላጎታችሁ መሆኑን ልብ ይሏል) የሚከፈላችሁ የሥራ ዋጋ ካለው የኑሮ ሁኔታና ውድነት ጋር ተመጣጣኝ ባለመሆኑ ኑሯችሁ እድገት አልባ መሆኑን የምትገነዘቡት ነው። በተለይም ደግሞ በኑሮ ውድነቱ የተነሳም እንደ ሌላው የሕብረተሰብ ክፍል ሁሉ ክፉኛ እየተጠቃችሁ ያላችሁት እናንተ ናችሁ። መሠረታዊ የሆኑ አንዳንድ ምርቶች ላይ በተወሰነ አጋጣሚ ዋጋቸው ሊቀንስ የሚችል ሁኔታ ቢያጋጥምም እነዚህን ምርቶች ግብአት አድርገው የሚመረቱ ምርቶች ላይ የዋጋ ቅነሳ ስለማይታይ ለችግር ጊዜ ተብሎ የሚቀመጥ ሃብት የሌላችሁ ናችሁና በዚሁ እየተጎሳቆላችሁ የምትገኙት ቁጥራችሁ በርካታ ነው። ስለሆነም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ በሚሄደው ሰው ሰራሽ በሆነ የኑሮ ውድነት በናንተ ላይ እያሳረፈው ያለው ጫና ከፍተኛ ነው። ይህን ደግሞ በፆም በፀሎት የምትገላገሉት አልሆነም።

እነዚህ ባዕዳኖች እያረሱ ያሉበትን አካባቢ የተፈጥሮ ሁኔታ የሚንከባከቡ ሳይሆኑ ይበልጥኑ ጉዳት እያደረሱ ለመሆናቸው፤ የዛፍ ምንጠራው ለመሬት መሸርሸር፣ ለአካባቢው መጎሳቆል ዋና ምክንያት መሆኑን ባለሙያዎች ጉዳቱ ከቁጥጥር ውጭ ሳይሆን በፊት ከወዲሁ መፍትሄ እንዲፈለግ አቤቱታ እያቀረቡ ቢገኙም ከአገዛዙ በኩል ሰሚ አላገኙም። በዚህም ምክንያት የአየር ንብረት ለውጥ ባስከተለው ተፅዕኖ ሳቢያ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች በበርካታ ችግሮች ተተብትባችኋል። የግጦሽ መሬታችሁ ሳር ባለማብቀሉ የከብቶቻችሁ ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ እያስከተለ ያለው ውጤት ለልጆቻችሁ የሚሆን ወተት አለማግኘትና በጤንነታችሁ ብቻ ሳይሆን በሕይወታችሁም ላይ እያንዣበበ ያለውንም አደጋ ከናንተ በላይ የሚያውቅ ሊኖር አይችልም። ለዚህ ተመጣጣኝ የሆነ እርዳታ ከአገዛዙ መጠበቅ ‘ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ’ በሚል



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

የሚገለጽ ነው። ታዲያ ‘በዚህ ሁኔታ እስከ መቼ ይዘለቃል?’ የሚለውን ደጋግመን የምናነሳው በነዚሁ ምክንያቶች እንጂ በሌላ አይደለም።

ዛሬ ደርግ ወድቆ የወያኔ አገዛዝ ከተተካ ከ18 አመት በኋላ የተረፋችሁ ምንድን ነው? ተብላችሁ ብትጠየቁ መልሳችሁ መበደል፤ መጨቆን፤ በጎጥ መከፋፈል፤ በድህነትና እርዛት መጠበስ፤ መሰረታዊ ፍላጎቶችን መነፈግ፤ መሰረታዊ ንፅህና በጎደለው ሁኔታ አሁንም ለመኖር መገደድ፤ ንፁህ የመጠጥ ውሃ አለማግኘት፤…ወዘተ መልሳችሁ እንደሚሆን ጥርጥር የለንም። ይህ ሁናቴ እንዲቀጥል ደግሞ በዘንድሮው የምርጫ ቲያትሩ ድምጻችሁን በግዴታ ለሱ እንድታደርጉ የተለያዩ ዘዴዎች አዘጋጅቶ ባሰማራቸው ሰላዮቹና ጆሮ ጠቢዎቹ አማካኝነት በአይነ ቁራኛ እየተመለከታችሁ መሆኑን የምታዩት ነው።

ይህንን ለአንዴም ለሁሌም ለመግታት የተመቻቸ ሁኔታ እንዳለ ደግሞ የምታስተውሉት ነው። በመሆኑም ለወደፊቱ የናንተን ፍላጎትና ጥቅም ሊያስከብር በማይችል የምርጫ ቀልድ ተካፋይ እንድትሆኑ የሚደረግባችሁን ጫና በመቋቋም መንቀሳቀስ ከናንተ የሚጠበቅ ሀገራዊ ግዴታ ነው ብንል ሀቁን መናገር ነው የሚሆነው። እናንተ የትግሉ ደጀን አንዱ ናችሁና ወያኔን ከሥረ መሠረቱ ከጫንቃችሁ ለማውረድ ትችሉ ዘንድ ይፋዊም ሆነ ሚስጢራዊ በሆነ ሁኔታ ተደረጅታችሁ እንድትታገሉት ኢ.ሕ.አ.ፓ የትግል ጥሪውን ያቀርብላችኋል። ነፃነታችሁን ለመጎናፀፍ፡ ፍላጎታችሁንና ጥቅማችሁን ለማስከበር በምታደርጉት ትግል ኢ.ሕ.አ.ፓ ካሁን በፊት እንዳደረገው ሁሉ አሁንም ከጎናችሁ ነው። የሚከፈለውንም መስዋዕት አብሯችሁ የሚጋራው ነው። ነፃነትም ሆነ መብት የሚጥመውና ለዛም የሚኖረው በትግል ከጃችን ሲገባ ብቻ ነው። በችሮታ ድልን የተቀዳጀ ሕዝብ በውጭው ዓለምም ሆነ በሀገራችን ታይቶ አይታወቅም። የጣሊያንን ወራሪ የጦር ኃይል ላይ ድልን የተጎናፀፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ የሚያስተምረን ይህንኑ ነው። ያወረሱንም የጀግንነት ገድል ይህንኑ የሚያረጋግጥ እንጂ ሌላ አይደለም። ለኑሯችሁ መለወጥ የናንተን ተሳትፎ የግድ ይላልና ‘ተነሱ!’ አብረን ይህንን ጸረ ህዝብ ቡድን በጋራ እናስወግደው። ተረዳድተን ቆርጠን ከታገልነው ያስታጠቀው ሰራዊትም ሆነ የደህንነት ጠባቂዎቹ ከውድቀት አያድኑትም። እነሱም ቢሆን ሁኔታው ሲጠጥር ሽርተት ብለው ከሕዝብ ጎን መሰለፋቸው የማይቀር ነውና!

በትግል እንጂ በምርጫ ጨዋታ የአርሶ አደሩ ነፃነት አይከበርም!!
በተባበረ ትግል እናቸንፋለን!!



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France